www.ginbot7.org
# የግንቦት 7 ድምጽ
የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ቀን፤ሐምሌ 10 2000 ዓ.ም የግንቦት7 ድምጽ ቁጥር 9

## “በኢትዮጵያ ረሀቡና የኑሮ ውድነቱ እየተባባሰ ነው።"
## "ማጅራት ገትርና ተቅማጥ በስፋት ተከስቷል" (ሴቭ ዘ ችልድረን)
## “በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እንበላለን” (የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች)

በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ዕርዳታ እየተሰጠ ቢሆንም፤ ረሀቡና የኑሮ ውድነቱ እየከፋና እየተባባሰ መምጣቱ ተገለፀ። በተለይ በአማራ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች ረሀቡ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የገለፀው ሴቭ ዘ ችልድረን ዩኬ፤የ እህል ዋጋም እስከ ሶስት እጥፍ ድረስ ማሻቀቡን አመልክቷል።ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ከምግብ እህል ችግሩ ጋር በተያያዘ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እየበሉ ህይወታቸውን ለማቆየት መገደዳቸውን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተናገሩ።

የአዲስ አበባ፣ የአዋሳና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰሞኑን እንደገለፁት፤ ከኑሮ ውድነቱ ጋር በተያያዘ በዩኒቨርሲቲያቸው የነበረው የወትሮ የምግብ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል።

ከሳምንት ላላነሰ ጊዜ በተከታታይ ያለማቋረጥ የጓጎለ ሩዝ እንደሚቀርብላቸው የተናገሩት ተማሪዎቹ፣ ሁሉም፤ ወትሮ በማያውቁት ከባድ የጨጓራ ህመም እየተሰቃዩ መሆናቸውን በሀኪም በማረጋገጣቸው፤ ህይወታቸውን ለማቆየት ያህል በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ለመቅመስ መገደዳቸውን ገልጸዋል።

ስለ ጉዳዩ የተጠየቁት የየዩኒቨርሲቲዎቹ አስተዳደሮች፤ ችግሩ ከእነሱ አቅም በላይ እንደሆነና በዩኒቨርሲቲዎቹ ወቅታዊ አቅም ሊፈታ እንደማይችል ተናግረዋል።

ደፋሩ አዲሱ ለገሰ "የረሀቡን ወሬ እያባባሱት ያለው፤ ይህንን አስታከው በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እየለመኑ ኪሳቸውን መሙላት የሚፈልጉ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ናቸው፤ ችግሩ ከኛ ቁጥጥር እንደማይወጣ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ" ብሎ በአደባባይ መናገሩ ይታወሳል።

አርብቶ አደሮች በሚኖሩባቸው የሶማሌ ዞኖች የውሀ ቢርካዎች ደርቀዋል፣ የግጦሽ ሳር ጠፍቷል፤ በዚህም ሳቢያ ከብቶች የሚበሉት አጥተው እየሞቱ ነው’ ብለዋል-የድርጅቱ ተወካይ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁኔታው እየተባባሰ እንጅ እየተሻሻለ ሊመጣ አልቻለም ያሉት የሴቭ ዘ ችልድረን ተወካይ፤ ድርቁ በከፋባቸው አካባቢዎች የማጅራት ገትር፣የተቅማጥና የኩፍኝ በሽታዎች በስፋት መከሰቱ ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ አድርጎታል ብለዋል።